የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-[illegible]@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. መአድ/3/57/2003
ቀን
Date 1/3/2003

# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/
# ጋዜጣዊ መግለጫ

## በአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ ሪፖርት ላይ የተሰጠ

የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ ሁለት ወር ከአንድ ሳምንት ያክል የምርጫውን ሂደት፣ የምርጫውን ቀንና የድምጽ ቆጠራውን መታዘቡን ገልጾ ስለምርጫው ግምገማውን ያቀረበው በአራት አካላት ከፋፍሎ ነው ማለት ይቻላል፡፡

1. **ማጠቃለያ**

   የምርጫውን ሂደትና ውጤት ሲያጠቃልል የሚከተለውን ብሏል፡፡
   - የምርጫ ሂደቱ ዓለም አቀፋዊ ደረጃ ያላሟላ ነው ካለ በኋላ እንደሚከተሉው አብራርቷል፡፡
   - ምርጫው ግልጽነት፣ ነጻነት እና ፍትሐዊነት ይጐድለዋል፡፡ የፖለቲካ መወዳደሪያ ሜዳ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት እንዲያገለግል አልተደረገም፤ ሚዛናዊነት የጐደለውና እጅግ በጣም ለገዢው ፓርቲ ያደላ ነበር ብሏል፡፡

2. **ገዢውን ፓርቲ በማስመልከት የሚከተሉትን ደምድሟል**
   - የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት እና እርሱን ተከትለው የወጡት አዋጆች (የምርጫ ቦርድ አዋጅ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ሕግ) እና ሌሎችም ሕጐች ሰብአዊ መብት እንዲከበር፣ ምርጫው ግልጽ፣ ዲሞክራሲያዊና ፍትሐዊ እንዲሆኑ እንዲሁም የሕዝብ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል በነጻነት የመንቀሳቀስና ራሳቸውንና ፓርቲያቸውን የማስተዋወቅና የመግለጽ መብት የሚያረጋግጡላቸው ቢሆኑም በምርጫው አተገባበር እነዚህ ሕጐች ተግባራዊ አልተደረጉም ብሏል፡፡

በአጠቃላይ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመላ ሀገሪቱ የመሰብሰብ፣ ራሳቸውን የማስተዋወቅና የመንቀሳቀስ ነጻነት አልተከበረላቸውም፡፡ በተቃራኒው የገዢው ፓርቲ በመላ ሀገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ ራሱን እንደፈለገው አንቀሳቅሷል፣ አስተዋውቋልም ብሏል፡፡ በተጨማሪም፡-

- በገዢው ፓርቲና በመንግሥት አካላት መዋቅርና አስተዳደር መካከል ልዩነት የለም፣
- ገዢው ፓርቲ የመንግሥትን ንብረት፣ የቀበሌን ጽ/ቤቶች ጨምሮ፣ ሥልጣኑን መከታ በማድረግ መጠቀሙን የአውሮፓ ታዛቢ ቡድን ተመልክቷል፣ ተገንዝቧልም፣ ብሏል፣
- በምርጫው ዕለት የድምጽ ቆጠራው ግልጽ አልነበረም፣
- ከእየ ክልሉ የመጡት የተጠቃለሉ የድምጽ ቆጠራ ውጤቶች በምዝገባ ወቅት ከተመዘገቡት ጋር አይጣጣሙም፣
- የምርጫ ካርዶች ተሰርዘው፣ ተደልዘው፣ ታርመዋል፣
- ከብዙ ቦታ የተላኩት የምርጫ ውጤት መሙያ ቅጾች በትክክል አልተሞሉም፣
- የምርጫው ሂደትም ሆነ ቆጠራው ግልጽነት ስለሚጐድለው አመኔታ የለውም፣
- የምርጫውን ሂደት ጥሰቶች ሲያብራራ ምርጫው ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማስፈራራት፣ ድብደባ እና [እስራት] የደረሰባቸው በመሆኑ በገዢው ፓርቲ፣ በመንግሥት አስተዳዳሪዎች እና አልፎ አልፎም በፖሊሶች ላይ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛና አሳሳቢ የሆነ ወቀሳ መሰንዘራቸውን በመረዳት በሪፖርቱ እንዲንፀባረቅ ተደርጓል ካለ በኋላ እነዚህን ችግሮች ለመቀነስ ወይም ለመፍታት ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት እርምጃ አልወሰዱም ብሏል፡፡

3. የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድንም ምርጫው ግልጽ፣ ነጻ፣ ዲሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ባለመሆኑ ኮንኖታል፡፡ ይህንንም አስተያየቱን እንደሚከተለው ያብራራል፡፡

- የምርጫ ቦርድ የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት በሚገባ አልመራውም ካለ በኋላ የምርጫ ሕጉና የመሠረታዊ መመሪያዎች አጠቃቀም ብዙ አሉታዊ ክንዋኔዎች ታይተውባቸዋል ብሏል፡፡ በዚህም ምክንያት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእርሱ ላይ የነበራቸውን እምነት ማጣት መለወጥ አልቻለም፣ ቦርዱ ተአማኒ አልነበረም ብሏል፡፡
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሌሎች ግድፈቶች ሲያስርዳ እንደሚከተለው ብሏል፣
    - ምርጫ አስፈጻሚዎች በእየ ደረጃው በቂ ሥልጠና አልተሰጣቸውም፣
    - የምርጫ ምዝገባ ወጥ አልነበረም
    - የምርጫ ጣቢያዎች ዝርዝር የተሟላ አይደለም፣
    - የመራጮች ምዝገባ በኮምፒዩተር ያልታገዘ በመሆኑ መራጮች በድግግሞሽ ላለመመዝገባቸው መተማመኛ የለም፣

- ቦርዱ ሕዝባዊ ድርጅቶች መራጮችን በማስተማር እንዲሳተፉ ባለማድረጉ በጐ አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ ከልክሎአቸዋል፣ ይህም በመሆኑ በምርጫው ላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ ሊደርስ ችሏል ብሏል፡፡
- ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተመደበው ገንዘብ ዝቅተኛ ነው ብሏል፣

4. የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ስለ መገናኛ ብዙኃንም ግምገማውን እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

- የግል ሚዲያ ገለልተኛ ቢሆኑም የመንግሥት ሚዲያ ግን ሚዛናዊ ዜና አያቀርቡም ነበር፡፡ ከግማሽ በላይ በሁሉም የሚዲያ መስኮች ማለትም፤ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጦችና በመጽሔቶች የኢህአዴግን የምርጫ ዘመቻ ነበር የዘገቡት፡፡ ዜና ሲዘግቡም በጥንቃቄ ነበር የሚያቀርቡት፡፡ [በሌላ አነጋገር ፍርሃት ነበረባቸው ማለት ነው]፡፡
- የአሜሪካ እና የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያዎች በመንግሥት እንዲታፈኑ በመደረጋቸው ምክንያት መራጩ ሕዝብ ከተለያዩ አካባቢዎች ሚዛናዊ መረጃ ለማግኘት አልቻለም ብሏል፡፡

5. በመጨረሻም የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን የመሰለውን የመፍትሔ ሀሳብ እንደሚከተለው በሦስት ክፍሎ አቅርቧል፡፡

### 5.1. ገዢውን ፓርቲ በሚመለከት

- የፖለቲካ ሜዳ ለሁሉም ተወዳዳሪዎች በእኩል የሚንቀሳቀሱባት መሆን አለበት፤
- የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ እንዲጎለብት ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው፣
- ከሀገር የተሰደዱት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአመራር አባላት [እና ሌሎችም] ወደ ሀገር እንዲመለሱ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡
- ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የገንዘብ ዕርዳታ እንደገና ሊታይ ይገባዋል፡፡
- በገዢው ፓርቲና በመንግሥት የአስተዳደር መዋቅር ፍጹም ግልጽ የሆነ ልዩነት መኖር አለበት፡፡
- ገዢው ፓርቲ ታማኝ መሆን አለበት፡፡
- ገዢው ፓርቲና መንግሥት ሥልጣናቸውን መከታ ማድረግ የለባቸውም፡፡
- ገዢው ፓርቲ የመንግሥትን ሀብት ለፓርቲ ሥራ መጠቀም የለበትም፡፡

### 5.2. ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሚመለከት

- የምርጫ ቦርድ ከገዢው ፓርቲና ከማንም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገለልተኛ ሆኖ ኃላፊነቱን በነፃነት መወጣት አለበት፡፡ ይህም ማለት የምርጫውን ሂደት ግልጽ፣ ነፃ፣ ፍትሐዊ እና ተአማኒ ለማድረግ ገለልተኛ ሆኖ ሁሉንም ተፎካካሪዎች በእኩል ማገልገል አለበት፡፡
- የምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈጻሚነት የመንግሥት ሠራተኞች መጠቀም የለበትም፡፡ ራሱን ችሎ እንዲሰራ በቂ በጀት ሊመደብለት ይገባል፡፡
- የመራጮች ምዝገባ በኮምፒውተር ሊታገዝ ይገባል፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ" ሥራ አመራር ጽ/ቤት ALL ETHIOPIAN UNITY PARTY (AEUP)

- የምርጫ ቦርድ ቋሚ ብሔራዊ የምርጫ ምዝገባ ሥርዓት ሊፈጥር ይገባል፡፡
- ማናቸውም ምርጫን አስመልክቶ የሚዘጋጁ መረጃዎች ለሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት መስጠት አለበት፡፡

## 6. የመኢአድ አቋም

ኢህአዴግ መስሎት ነው እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምጽ ዘርፎ ሕዝብ መረጠኝ ብሎ ቢመጻደቅ እና መንግሥት ቢመሰርት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅር እንዳላለው ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ውሎ አድሮም ጊዜው ሲደርስ ተጠያቂ የሚሆንበት ቀን እንደሚመጣ ተገንዝቦ ያች የቁርጥ ቀን ከመድረሷ በፊት ዛሬውኑ ስሕተቱን አርሞ ምርጫው የሚደገምበትን እና መኢአድ ግንቦት እና ነሐሴ ወሮች 2002 ዓ.ም ውስጥ ባወጣቸው መግለጫዎች የጠየቃቸውንና ባጭር ባጭሩ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ውሎ ሳያድር እውን እንዲያደርግ ከእውነተኛ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ምክክርና ድርድር እንዲያደርግ መኢአድ ያሳስባል፡፡

መኢአድ ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት በተራድኦ ለፈፀሙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ጥሰቶች እና ወደፊት በሀገራችን የመንግሥት ሽግግር በሰላማዊ መንገድ መከናወን እንዲችል ኢህአዴግ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንዲወሰድ እንጠይቃለን፡፡

- 2002 ዓ.ም ምርጫ ማግሥት ጀምሮ ገዢው ፓርቲና መንግሥት በመኢአድና በሌሎች ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ እያደረሱ ያሉት ማስፈራራት፣ ዛቻና ስጋት በአስቸኳይ ይቁሙ!
- በዚሁ ምርጫ ማግሥት መሬታቸውን የተነጠቁትና የተሰደዱት የመኢአድ አባላትና ደጋፊ ገበሬዎች መሬታቸው ተመልሶላቸው በሰላምና በፍቅር በቀዬአቸው እንዲኖሩ ይደረግ፡፡
- በዚሁ ምርጫ ማግሥት በመንግሥት ትዕዛዝ ከሥራቸው የተፈናቀሉት የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች ከተባረሩበት ቀን ጀምሮ ደሞዛቸው ተከፍሎአቸው ይቅርታ ተጠይቀው ወደ ሥራቸው እንደመለሱ አፋጣኝ እርምጃ ይወሰድ፣ ወደፊት ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈፀምም ጥብቅ መመሪያ ለፌደራል እና ለክልል አካላት ሁሉ እንዲተላለፍ ይደረግ፡፡
- ከእነዚህ ጐን ለጐን ገዢው ፓርቲና መንግሥት ለፈፀሙት ስድስቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር የሕግ ጥሰቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና የግል ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ኢህአዴግ ይቅርታ ይጠይቅ፡፡
- በምርጫው ሂደት በአካል ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች ኢህአዴግ ካሳ ይክፈል፡፡
- ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ኢህአዴግ በአስቸኳይ ከእውነተኛ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ውይይትና ድርድር ያድርግ፡፡
- ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት በሰፈረው መሠረት የሚዲያን ነጻነት ያክብር፡፡ ከአግባብ ውጭ የሥራ ፈቃዳቸው የተሰረዘባቸው የግል ጋዜጦችና አሳታሚዎች ፈቃዳቸው በአስቸኳይ ይመለስላቸው፡፡ መንግሥታዊ የሚዲያ ድርጅቶች ወደ ግል ድርጅትነት በአስቸኳይ ይዛወሩ፡፡

የግል ድርጅቶች የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማቋቋም እንዲችሉ በአስቸኳይ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰድ፡፡ የግል ሚዲያ ከመንግሥታዊ ድርጅቶች መረጃ የማግኘት ሕጋዊ መብታቸው ይከበር፡፡ እነዚህንና ሌሎች አስፈላጊ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚዲያ ሕግ በአስቸኳይ እንዲሻሻል ይደረግ፡፡

- ገዢው ፓርቲና መንግሥት የሕዝብን መደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመናገር እና የመጻፍ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ካለገደብ ያክብሩ፡፡
- ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም የሀገራችን ክልል ያለገደብ ቢሮ ከፍተውም ሆነ ሳይከፍቱ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው እንዲከበር ለሁሉም ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች አስፈላጊው መመሪያ በአስቸኳይ ይተላለፍ፡፡
- ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም የሀገራችን ክልል ከሕዝቡ ጋር በፈለጉበት ሁኔታ፣ በአዳራሽ ውስጥ፣ በሕዝብ ሥፍራ፣ በሰላማዊ ሰልፍ ተሰብስበው ካለአንዳች ገደብ መወያየት እና ቅሬታ ማሰማት እንዲችሉ አስፈላጊው መመሪያ ለሚመለከተው ሁሉ በአስቸኳይ ይተላለፍ፡፡
- ማንኛውም ብሔረሰብ በፈለገበት ክልል፣ ግብርናን ጨምሮ፣ በፈለገበት የሥራ መስክ ተሠማርቶ ንብረት ማፍራት እንዲችል ሕገ-መንግሥታዊ መብቱ ይከበርለት፡፡
- የምርጫ ቦርድ እና ሥራ አስፈጻሚዎች ከማናቸውም ተፎካካሪ ፓርቲ በነጻነት እና በገለልተኝነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ይከበር፡፡
- የፍትሕ አካላትም /ማለትም ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግና ዳኞች/ እንዲሁ በነጻነትና በገለልተኛነት ቃል የገቡትን ኃላፊነት እንዲወጡ ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ይከበር፡፡
- የመከላከያ ኃይል እንዲሁ በነጻነትና በገለልተኝነት ቃል የገቡትን ኃላፊነት እንዲወጡ ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ይከበር፡፡
- የገዢው ፓርቲ መዋቅር ከቀበሌ ጽ/ቤቶች ጀምሮ ከማናቸውም የመንግሥት እና ሕዝባዊ ጽ/ቤቶች ወጥቶ የመንግሥት ሠራተኞች እና መንግሥታዊ አገልግሎቶች ከገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ እንዲላቀቁ አስቸኳይ እርምጃ ይወሰድ፡፡

***ኢትዮጵያ በትግላችን ለዘለዓለም ትኖራለች!***

***የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/***
***አዲስ አበባ***
***ሕዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም***